በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን 07 2011
Date
ቁጥር 1/147/11
Ref.No

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ:- <u>የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ ይመለከታል፤</u>

የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 147/2011 ሆኖ የጸደቀ መመሪያ ከዚህ ጋር በማያያዝ የተላከላችሁ ስለሆነ በመመሪያው መሰረት እንዲፈጸም አሳስባለሁ።

ከሰላምታ ጋር

አዳነች አበቤ
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ፤</u>

- ✓ ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ✓ ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ✓ የታክስ ህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ✓ ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ

<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

የበለፀገች
ኢትዮጵያ!

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: +251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www.erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ግብር ከፋች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች

<u>አዲስ አበባ</u>

- ለመቀሌ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት /መቀሌ/
- ለአዳማ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት / አዳማ/
- ለባህርዳር ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት /ባህርዳር/
- ለድሬደዋ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት /አዳማ/
- ለሐዋሳ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት /ሐዋሳ/
- ለኮምቦልቻ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት /ኮምቦልቻ/
- ለጅማ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት /ጅማ/

የገቢዎች ሚኒስቴር

Ministry of Revenues

# የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 147/2011

**መጋቢት /2011 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 147/2011

እዳቸውን ከፍለው ላጠናቀቁ ወይም በመክፍል ላይ ላሉ ታክስ ከፋዮች የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ስለሚሰጥበት ሁኔታ መወሰን በማስፈለጉ፣

የገቢዎች ሚኒስቴር በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 61(2) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 147/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

1/ **"የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት"** ማለት አንድ ታክስ ከፋይ የታክስ ክፍያ ግዴታውን መወጣቱን ወይም እየተወጣ መሆኑን የሚገልጽ ከታክስ ባለስልጣኑ በጽሁፍ የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፡፡

2/ **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት ታክስ ከፋዩ ሊያስወግደው የማይችል በተፈጥሮ ወይም በሰዉ ሰራሽ ምክንያት በተወሰነ አካባቢ የሚከሰት ወይም የተነሳ ጦርነት፣ የመድን ሽፋን የሌላቸውና በንግድ ስራው ላይ ጫና የሚፈጥር እንደ ዝርፊያ፣ ጐርፍ፣ ቃጠሎ፣የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች የመሳሰለ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም ወይም ሞት ሲሆን በድርጅት ወኪሎችና እንደራሴዎች የደረሰ ጽኑ ህመም ወይም ሞትን ይጨምራል፡፡

3/ **"ጽኑ ህመም"** ማለት በታክስ ማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ ተንቀሳቅሶ መስራት የማያስችልና በታወቀ የህክምና ተቋም የሚረጋገጥ ከባድ ህመም ነው፡፡

4/ **"ከፍተኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በታክስ ጊዜው ውስጥ የታክስ ባለስልጣኑ በስጋት መምረጫ መስፈርትን መሰረት በማድረግ ታክስ ከፋዩን የሚመድብበት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ነው፡፡

5/ **"መካከለኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በታክስ ጊዜው ውስጥ የታክስ ባለስልጣኑ በስጋት መምረጫ መስፈርትን መሰረት በማድረግ ታክስ ከፋዩን የሚመድብበት መካከለኛ የስጋት ደረጃ ነው፡፡

6/ **"ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በታክስ ጊዜው ውስጥ የታክስ ባለስልጣኑ በስጋት መምረጫ መስፈርትን መሰረት በማድረግ ታክስ ከፋዩን የሚመድብበት ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ነው፡፡

7/ **"አጠቃላይ ኦዲት"** ማለት ኦዲት የሚያስፈልገው የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አገልግሎት የጠየቀ ታክስ ከፋይ የሒሳብ መግለጫና ደጋፊ ሰነዶች እንዲያቀርቡ በማድረግ መከፈል የሚገባው ያልተከፈለ ታክስ ስለመኖሩ ዝርዝር ወይም ጥልቅ የሒሳብ ምርመራ የሚደረግበት ስርዓት ነው፡፡

8/ **"አገልግሎት ኦዲት"** ማለት የሰነድ ማረጋገጫ የሚያስፈልገው የክሊራንስ አገልግሎት የጠየቀ ታክስ ከፋይ በታክስ ባለስልጣኑ የሚገኝ መረጃ እና እንደአስፈላጊነቱ ከሶስተኛ ወገን ከሚገኙ መረጃዎች ጋር በማመሳከር መከፈል የሚገባው ያልተከፈለ ታክስ ስለመኖሩ የሚደረግ የሂሳብ ምርመራ ስርዓት ነው፡፡

9/ **"የንግድ ሥራ ሀብት"** ማለት የንግድ ሥራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ ሀብት ነው፡፡

10/ **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡

11/ **"የታክስ ባለሥልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ማለት ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶቻቸውንም ይጨምራል፡፡

12/ **"ሚኒስቴር"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን የሚኒስቴሩን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይጨምራል፡፡

13/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላት በፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ እና በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

14/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀው ለሴትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

የገቢዎች ሚኒስቴር

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት በሚጠይቁ የታክስ ክፍያ ግዴታቸውን በተወጡ ወይም እየተወጡ ባሉ ወይም በሚወጡ ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የአገልግሎት ዓይነቶች፤

1/ የንግድ ስራ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃድ ለማደስ ወይም ለመመለስ፣

2/ በጨረታ ለመካፈል ወይም ለመሳተፍ፣

3/ ለተሽከርካሪዎች ወይም የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ /ከላውዶ/ ለማድረግ፣

4/ የባንክ ብድር ለማግኘት፣

5/ ለተሽከርካሪ ቅሪት የመድን ካሳ ለማግኘትና የሰሌዳ ለውጥ ለማድረግ፣

6/ የድርጅት ስም ወይም አድራሻ ለመለወጥ፣

7/ ጥቅም የሚከፈልበት የካፒታል ሃብት ለማስተላለፍ ፣

8/ ድርጅት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ለመዝጋት ወይም ዘርፍ ለመቀየር፣

9/ የባለቤትነት ስም ምዝገባ የሚያስፈልገውን የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላፍ፣

10/ ህጋዊ ህልውና የነበራቸው ድርጅቶች በአንድ ላይ ለማደራጀት ወይም ለማዋሀድ፣

11/ የንግድ መደብር ለሌላ አካል በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በውርስ ወይም በመሳሰሉት ለማስተላለፍ፣

12/ ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ስለመከፈሉ ለተቀጣሪው የሚሰጥ ማረጋገጫ፣

13/ የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ተጠቃሚ በትምህርት ዘመኑ የተጋራውን ወጪ በአገልግሎት ወይም በክፍያ ስለመወጣቱ የሚሰጥ ማረጋገጫ፣

14/ ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ለማግኘት፡፡

## 5. የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፣

1/ ማንኛውም ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ማሟላት የሚገባው ቅድመ ሁኔታ፣

(ሀ) የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው በጽሑፍ ጥያቄ ማቅረብ፤

(ለ) ውዝፍ የታክስ ዕዳ ወይም ወቅታዊ የታክስ ክፍያ የፈጸመ መሆን፣

(ሐ) ውዝፍ የታክስ ዕዳ ወይም ወቅታዊ የታክስ ዕዳ ለመክፈል የክፍያ ስምምነት የገባና በውሉ መሠረት እየተከፈለ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ፣

(መ) በደረሰው የታክስ ዉሳኔ ማስታወቂያ ላይ ቅሬታ ያለዉ ታክስ ከፋይ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የስራ ክፍል ወይም ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ለሚገኝ ፍርድ ቤት ቅሬታውን አቅርቦ በመታየት ላይ የሚገኝ ስለመሆኑ የጽሁፍ ማስረጃ ማቅረብ አለበት::

2/ ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው ቢኖርም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሳያሟላ ወይም ሳያረጋግጥ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ሊሰጠው አይችልም::

(ሀ) ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ እና ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ግብር ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ከፋዩ የታክስ ነፃ መብት ያለው ስለመሆኑ ወይም በግብር እፎይታ ጊዜ ላይ ያለ ስለመሆኑ ከሚመለከተዉ አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማስረጃ፣

(ለ) በታክስ ከፋይነት በግብር ዓመቱ ያልተመዘገበ ከሆነ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አለመዉሰዱ እና የታክስ ፋይል በስሙ አለመከፈቱ እስኪረጋገጥ፣

(ሐ) በንግድ ሥራ ፈቃዱ ምንም ዓይነት ሥራ አለመስራቱን የገለጸ ታክስ ከፋይ አለመስራቱ እስኪረጋገጥ፣

(መ) በኮንስትራክሽን ማሽነሪ ማከራየት ዘርፍ የተሰማራ ታክስ ከፋይ በታክስ ጊዜው ታክስ ያልከፈለው ማሽነሪው በመበላሸቱ ምክንያት መሆኑንና ይህንኑ በታክስ ህጉ መሠረት ማስታወቁን እና ለዚሁም በ3ኛ ወገን የተረጋገጠ ማስረጃ እስኪያቀርብ፣

(ሠ) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (መ) አፈጻጸም ታክስ ከፋዩ ለፈቃድና ቦሎ ማደሻ ክሊራንስ ሲጠይቅ የኮንስትራክሽን ማሽን በመበላሸቱ ምክንያት ያለመስራቱን በ30 ቀናት ውስጥ ማስታወቁ እስኪረጋገጥ፣

(ረ) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (መ) አፈጻጸም በፊደል (ሠ) ከተጠቀሰው በተጨማሪ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ለመሸጥ ከሆነ ማሽነሪው ከቆየበት ቦታ (ጋራዥ) ወይም ከቆመበት ቀበሌ አስተዳደር ማረጋገጫ ማስረጃ እስኪያቀርብና እስኪረጋገጥ፣

(ሰ) በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማራ ታክስ ከፋይ በታክስ ጊዜው ታክስ ያልከፈለው የተሽከርካሪው ሊብሬ እና ታርጋ ለመንገድ ትራንስፖርት በመመለሱ ወይም መድን ድርጅት ቅሪት አካሉን በመረከቡ ምክንያት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እስኪያቀርብ፣

(ሸ) የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ተጠቃሚ የአገልግሎት ግዴታውን የተወጣ ስለመሆኑ የጽሑፍ ማስረጃ እስኪያሟላ ወይም የሚፈለግበትን ክፍያ እስኪፈጽም ድረስ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት መስጠት አይቻልም።

(ቀ) በዚህ መመሪያ የተደነገገው ቢኖርም ከታክስ ከፋዩ የሚፈለገው ታክስ የሚሰበሰብ ስለመሆኑ ስጋት ሲኖረውና ታክሱ በአስቸኳይ መሰብሰብ ያለበት ሆኖ ሲገኝ ታክሱ ሳይሰበሰብ ለታክስ ከፋዩ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት መስጠት አይቻልም።

## 6. <u>ክሊራንስ ለመስጠት ኦዲት የማያስፈልጋቸው አገልግሎቶች</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጹት ሁኔታዎች እስከተሟሉ ድረስ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት አገልግሎቶች ታክስ ከፋዩን ኦዲት ማድረግ ሳያስፈልግ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል፡

(ሀ) ንግድ ስራ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃድ ለማደስ፣

(ለ) ጨረታ ለመካፈል ወይም ለመሳተፍ፣

(ሐ)ለተሽከርካሪዎች ወይም ለኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ /ክላውዶ/ ለማድረግ፣

(መ) የባንክ ብድር ለማግኘት፣

(ሠ) የመድን ካሳ ለማግኘትና የተሽከርካሪ ሰሌዳ ለውጥ ለማድረግ፣

(ረ) የድርጅት ስም ወይም አድራሻ ለመለወጥ፣

(ሰ) የንግድ ስራ ሀብት መቀነስን ሳይጨምር የንግድ ዘርፍ ቅነሳ፣

(ሸ) ድርጅቶች እንደገና ተደራጅተው ሲዋሀዱ የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳ አካቶ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ የፀደቀ ሰነድ ከቀረበ፣

2/ የክሊራንስ ጥያቄ በቀረበበት ጊዜ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የተሰጠው እና ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ያለበት ታክስ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (መ) መሰረት ኦዲት ሳይደረግ የባንክ ብድር እንዲወስድ ክሊራንስ የሚሰጠው ዕዳውን የከፈለ እንደሆነ ወይም ለመክፈል የባንክ ዋስትና ያቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ሊሰጠው የሚችለው፡

(ሀ) ታክስ ከፋዩ ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቂያ እና መክፈያ የመጨረሻ ቀን ከመድረሱ በፊት የንግድ ስራ ፈቃድ ለማደስ፣ በጨረታ ለመሳተፍ፣ የባንክ ብድር ለመውሰድ እና የጉዳት ካሳ ለማግኘት የሚቀርብ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ከሆነ ጥያቄው ከቀረበበት የግብር ዘመን በፊት ላሉት ጊዜያት ታክሱን አስታውቆ ግዴታውን የተወጣ ስለመሆኑ፣ እና

(ለ) የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የተጠየቀበትን አገልግሎት አይነትና የተፈለገበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ (መ) የባንክ ብድር ለማግኘት የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለጠየቀ ሰው የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ጥያቄ አቅራቢው የንግድ ሥራ ያልሰራና በግብር ከፋይነት ያልተመዘገበ ከሆነ የታክስ ባለሥልጣኑ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከመረጃ ቋት ተገቢውን ማጣራት አድርጎ ጠያቂው በንግድ ሥራ አለመሰማራቱን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) የተገለጸው ቢኖርም የንግድ ስራ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ሥራ ያልሠሩ ታክስ ከፋዮች የንግድ ስራ ፈቃድ ለመመለስ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከታክስ ባለስልጣኑ የስራ ክፍሎች እና ከሶስተኛ ወገን መረጃ በማጣራት የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

7. <u>የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት ኦዲት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች</u>

1/ የሚሸጠው ወይም የሚተላለፈው የንግድ ስራ ሀብት ከሃምሳ በመቶ ያነሰ ከሆነ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት አገልግሎት ኦዲት ስራ መከናወን አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) የተደነገገው ቢኖርም በከፍተኛ እና በመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የሚስተናገድ ታክስ ከፋይ በግብር ዘመኑ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ በሚከተሉት አገልግሎቶች ላይ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት አገልግሎት ኦዲት መደረግ አለበት፣

(ሀ) ከሃምሳ በመቶ በላይ የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፣

(ለ) ድርጅትን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመዝጋት፣

(ሐ) የንግድ ዘርፍ ለመቀየር ወይም ለመቀነስ ከሆነ፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (2) የተደነገገው ቢኖርም በከፍተኛ እና በመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የሚስተናገድ ታክስ ከፋይ በግብር ዘመኑ በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ በሚከተሉት አገልግሎቶች ላይ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት አጠቃላይ ኦዲት መደረግ አለበት፣

(ሀ) ከሃምሳ በመቶ በላይ የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፣

(ለ) ድርጅትን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመዝጋት፣

(ሐ) የንግድ ዘርፍ መቀየር ወይም መቀነስ ከሆነ፣

(መ) ድርጅቶች በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለመዋሀድ በውህደት የሚፈጠረው ድርጅት የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳን ለመክፈል ግዴታ ገብቶ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሰነድ ከቀረበ፣

(ሠ) የንግድ መደብሩን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በውርስ ለማስተላለፍ፣

4/ በየትኛውም የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ የአነስተኛ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሲጠይቅ ከሀምሳ በመቶ በላይ የሆነውን የንግድ ስራ ሀብቱን ወይም የንግድ መደብሩን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ፣

በስጦታ ወይም በውርስ ለማስተላለፍ ወይም የንግድ ስራውን ለማቋረጥ ካልሆነ በስተቀር በአገልግሎት አዲት ብቻ የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት የተገለፀው ቢኖርም የአነስተኛ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ታክስ ከፋይ ከሀምሳ በመቶ በላይ የሆነውን የንግድ ስራ ሀብቱን ወይም የንግድ መደብሩን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በውርስ ለማስተላለፍ ወይም የንግድ ስራውን ለማቋረጥ የክሊራንስ ምስክር ወረቀት ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ አጠቃላይ አዲት ተከናውኖ ዕዳ የሌለበት መሆኑ ሲረጋገጥ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀቱ ይሰጠዋል፡፡

## 8. የታክስ ዕዳ ስለመኖሩ ማጣራት እና የታክስ ስሌት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ ቁጥር (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ከመስጠቱ በፊት ለሚከተሉት አገልግሎቶች አስፈላጊው መጣራት መደረግ አለበት፡፡

(ሀ) ጥቅም የሚከፈልበት የካፒታል ሃብት ማስተላለፍ፣

(ለ) ድርጅቶች በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለመዋሀድ በውህደት የሚፈጠረው ድርጅት የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳን ለመክፈል ግዴታ ገብቶ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ የሚያስረዳ እና የቴምብር ቀረጥ የተከፈለበት ውል ከቀረበ፣

(ሐ) የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ግዴታን ስለመወጣት ማስረጃ ሲጠየቅ፣

(መ) ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ስለመከፈሉ፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (መ) መሰረት ለተቀጣሪ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ቀጣሪው የስራ ግብር የተከፈለ ስለመሆኑ ለታክስ ባለስልጣኑ በጽሑፍ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡

## 9. የስጋት ደረጃ ያልወጣላቸው አገልግሎት ጠያቂዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታ

1/ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 8፣ 9፣ 10 እና 11 የተገለፁትን አገልግሎቶች የሚጠይቁ ከሆነ የስጋት ደረጃ እንዲወጣላቸው ይደረጋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) መሰረት የስጋት ደረጃ የወጣላቸው ግብር ከፋዮች እንደ አግባብነቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (7) መሰረት ይስተናገዳሉ፡፡

3/ በዚህ መመሪያ ንዑስ ቁጥር 1 መሰረት በተሰራው የስጋት መስፈርት መምረጫ መሰረት በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የተመደቡት ታክስ ከፋዮች መረጃ ለታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እና ለስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በየወሩ ይላካል፡፡

## 10. የአገልግሎት ኦዲት ወይም አጠቃላይ ኦዲት ወይም የታክስ ስሌት ግኝትን መሰረት በማድረግ ስለሚሰጥ ውሳኔ

ማንኛውም ታክስ ከፋይ በዚህ መመሪያ መሰረት በአገልግሎት ኦዲት ወይም በአጠቃላይ ኦዲት ወይም የታክስ ስሌት ተከናውኖበት በግኝቱ መሰረት ሊከፈል የሚገባው የታክስ ዕዳ ያለበት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ዕዳውን ሳይከፍል ወይም የክፍያ ስምምነት ሳይገባ ወይም የባንክ ዋስትና ሳያሲዝ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አይሰጠውም፡፡

## 11. በልዩ ሁኔታ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(1) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ማህበራዊ በሆኑ ምክንያቶች ሚኒስትሩ ወይም የሚወክለው ኃላፊ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት በልዩ ሁኔታ እንዲሰጥ ሊወሰን ይችላል፡፡

## 12. የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የሚያገለግልበት ጊዜ

ለታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የሚያገለግለው፡-

1/ በጨረታ ለመሳተፍ ወይም ከባንክ የብድር አገልግሎት ለማግኘት ከሆነ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከ 6 ወር ድረስ ፣

2/ የንግድ ፈቃድ ለማሳደስ፣ተሽከርካሪን ለማስፈተሽ (ካላዉዶ ለማስደረግ) የሚሰጥ የታክስ ምስክር ወረቀት ከሆነ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ፡

(ሀ) በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ሂሳባቸውን ለሚዘጉ እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ፣

(ለ) ሂሳባቸውን በራሳቸው የሂሳብ ጊዜ ለሚዘጉ እስከ ሂሳብ ጊዜያቸው ማጠናቀቂያ ቀን ድረስ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

3/ የንግድ ስራቸውን በከፊል ወይም በሙሉ ለማቋረጥ፣ የባለቤትነት ስም ለውጥ ለማድረግ ወይም የንግድ ሀብትን ለማስተላለፍ የሚሰጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ከሆነ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሦስት ወራት፣

4/ የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ክፍያን በአገልግሎት ወይም ገንዘብ በመክፈል ግዴታውን የተወጣ ተጠቃሚ የሚሰጠዉ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የትምህርት ማስረጃውን ለመቀበል ብቻ ያገለግላል፡፡

5/ የታክስ ከፋዮች ምዝገባ እና ስረዛ ዳይሬክቶሬት ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ የተለያዩ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ቅጾችን እንደየአገልግሎት አይነቶች በመለየት ያዘጋጃል፡፡

## 13. <u>የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

ሚኒስትሩ፡-

1/ በአንቀጽ 6፣ 7(1) እና 8 በተገለጸው መሠረት ታክስ ከፋዩ ቅድመ ሁኔታውን የፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ ለታክስ ከፋዩ ማመልከቻውን ባቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት መስጠት የማይቻልበት ምክንያት ካለ ማመልከቻውን ባቀረበ በ 14 ቀናት ውስጥ የማይሰጥበትን ምክንያት በጽሁፍ መልስ መስጠት አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ለመስጠት አጠቃላይ ወይም አገልግሎት ኦዲት የሚያስፈልገው ከሆነ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን አንስቶ ባለው በዘጠና ቀናት ውስጥ ኦዲቱ ተጠናቆ ዉጤቱ የሚገለጽለት ስለመሆኑ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተገለጸው ጊዜ ውስጥ የታክስ ክሊራንስ ለጠየቀ ሰው በጽሁፍ ምላሽ ያልሰጠ ሰራተኛም ሆነ ኃላፊ ቅሬታ ሲቀርብበት ባሉት የሰራተኛ አስተዳደር ህጎች ተጠያቂ ይሆናል ፡፡

## 14. ቅሬታ ስለማቅረብ

ከታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በሚኒስትሩ አሰራር ላይ ቅሬታ ያለው ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለቅ/ጽ/ቤቱ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ስራ ክፍል ማቅረብ ይችላል፡፡

## 15. የተሻሩ መመሪያዎች

1. በመመሪያ ቁጥር 55/2003 የግብር ግዴታን ስለመወጣት በማረጋገጫነት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት (ክሊራንስ) አሰጣጥ በተመለከተ የተደነገገው ክፍል፣
2. በታክስ ክሊራንስ ጥያቄ በቅድሚያ ኦዲት መደረግ ያለባቸውና የሌለባቸው ግብር ከፋዮችን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 128/2009 ፣ እና
3. የታክስ ክሊራንስ አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 139/2010 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ቀደም ሲል ተጀምረው ፍጻሜ ያላገኙ ጉዳዮች ሲሰራበት በነበረው መመሪያ መሰረት ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

## 17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣...... ቀን 2011 ዓ.ም

አዳነች አቤቤ
የገቢዎች ሚኒስቴር
ሚኒስትር